**የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ**

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

**2015 ግንቦት ቅጽ 1 ቁጥር 10**


## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በከገበሬው ሱቆቹ ተጨማሪ የካፌና ሬስቶራንት አገልግሎቶችን ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑ ተገለጸ።

ምርትና ምርታማነትን በመጨመር የኑሮ ውድነትን ታሪክ ለማድረግ የሚሠራው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በሁሉም ከገበሬው የችርቻሮ ሱቆች ሲያቀርብ ከቆየው የግብርና እና የግብርና ማቀነባበሪያ ውጤቶች ሽያጭ በተጨማሪ ዓድዋ ድልድይ በሚገኘው የከገበሬው ሱቅ የካፌና ሬስቶራንት አገልግሎቶችን ለመስጠት እንዲሁም በሰሚት ቅርንጫፍ የጁስ ምርቶችን ለማቅረብ እንቅስቃሴ መጀመሩን የሪቴል ክፍል ኃላፊ ወ/ሮ ትዕግስት አስመላሽ አስታውቀዋል።

ከዚህ ቀደም በዓድዋ ድልድይ የከገበሬው ሱቅ ሲቀርብ የቆየው የካፌና ሬስቶራንት አገልግሎት በተለያዩ ምክንያቶች መቋረጡን ያወሱት ኃላፊዋ በቅርቡ ከበርካታ የመልሶ ግንባታ እና የማሻሻያ ዝግጅቶች በኋላ በተደራጀ መልኩ ወደ ተግባር ሊገባ መሆኑን እንዲሁም በሰሚት ቅርንጫፍ የከገበሬው ሱቅ ፍሬሽ ጁሶችን ለደንበኞች ማቅረብ ሊጀምር መሆኑን ይፋ አድርገዋል።



ምስል በነብዩ ዳንኤል

> **በሁለቱም መደብሮች የሚጀመሩት የፍራፍሬ ጭማቂ እንዲሁም የምግብና መጠጥ አገልግሎቶች ተፈጥሯዊ በሆኑና እና ከፍተኛ ጥራት ባላቸው የከገበሬው ምርቶች የሚዘጋጁ መሆናቸውን የገለጹት ወ/ሮ ትዕግስት ሁለቱም ፕሮጀክቶች ቅድመ ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደ ተግባር ሲገቡ መልካም የሥራ አጋጣሚ መፍጠር የሚችሉ መሆኑንና ለድርጅቱም ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያስገኙ መሆናቸውን አስረድተዋል።**

በተጨማሪም ኩባንያው ከፍተኛ ጥራት ባላቸው የግብርና ምርቶች ስርጭት ረኃብን ለመዋጋት ብሎም የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን የጥቁሮችን ኢኮኖሚያዊ የበላይነት ለማረጋገጥ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የሪቴል ዲፓርትመንት የበኩሉን ኃላፊነት እንደሚወጣ አስታውቀዋል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ መዲናችን አዲስ አበባን ጨምሮ በወላይታ ሶዶ፣ አርባ ምንጭ፣ ባሕር ዳር፣ ሐዋሳ፣ በቆጂ እና ጎንደር ከተሞች ላይ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ሲሆን የግብርና ዘርፉን በመደገፍ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን አምርቶ በችርቻሮ ሱቆቹ በማከፋፈል ሸማቹን ከገበሬው ጋር በቀጥታ የማገናኘት ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ተገልጿል።

ኩባንያው አሁን ላይ ባሉት 7 የችርቻሮ መሸጫ ሱቆች በአዲስ አበባ አትላስ፣ ላፍቶ፣ ቡልቡላ፣ ሰሚት፣ አያትና ዓድዋ ድልድይ አካባቢዎች ተደራሽ መሆን የቻለ ሲሆን በተጨማሪ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ወላይታ ሶዶ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የእንስሳት ተዋጽዖዎችን እንዲሁም ጥራት ያላቸው የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ላይ መሆኑም ተወስቷል።

በመጨረሻም ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በመላ አገሪቱ ነሺህ የችርቻሮ ሱቆችን በመክፈት ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የግብርናና የኢንዱስትሪ ውጤቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ማኅበረሰብ በማድረስ የኑሮ ውድነትን ታሪክ ለማድረግ ዕቅድ ይዞ እየሠራ ይገኛል ያሉት የሪቴል ክፍል ኃላፊዋ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በሚሰማራባቸው ይበልጥ ውጤታማ በሚያደርጉት አዳዲስ የንግድ ሥራዎች ሁሉ አገልግሎቱን በተቀላጠፈ መንገድ በመስጠት ኃላፊነቱን ይወጣል ሲሉ ሐሳባቸውን ገልጸዋል።

## ቴሌ ብር በ6ቱም የፐርፐዝብላክ ከገበሬው ሱቆች ቴሌብርን ተጠቅመው ለሚገበያዩ ደንበኞች የ10 በመቶ ቅናሽ ማዘጋጀቱን አስታወቀ።

ቴሌ ብር በሁሉም የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከገበሬው ሱቆች ቴሌ ብርን ተጠቅመው ለሚገበያዩ ደንበኞች ለአንድ ወር የሚቆይ የ10 በመቶ ቅናሽ ማድረጉን የፐርፐዝብላክ ዲጂታል አዶፕሽን ማናጀር ወ/ሪት ሩት ጉብሩ አስታውቀዋል።

'ኢትዮቴሌኮምና ፐርፐዝበላክ ኢትዮጵያ በአጋርነት ሲሠሩ መቆየታቸውን የገለጹት ማናጀሯ ኢትዮቴሌኮም የቴሌ ብር መተግበሪያን ካስተዋወቀ ጀምሮ የዘረጋው ዘመናዊ የሆነ የክፍያ ሥርዓት የተጠቃሚውን የዕለት ተዕለት የግብይት እንቅስቃሴ ቀላል ከማድረግ ባለፈ ለዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ትልቅ አስተዋጽዖ እያበረከተ መቆየቱን ነው የተናገሩት።

ከዚህ ቀደም ለፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አክሲዮን ግዢ እና የምርቶችን ግብይት ክፍያ ለመፈጸም የኩባንያው ደንበኞች ይገለገሉበት የነበረው ቴሌብር አሁን ደግሞ በምርቶች ሽያጭ ላይ የ10 በመቶ ቅናሽ ማቅረቡን ተከትሎ "ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከክፍያ መፈጸሚያ ድርጅቶች ጋር በአጋርነት በመሥራቱ ሊያገኛቸው ከሚችላቸው ጥቅሞች መካከል ለሠራተኞችና ለደንበኞች የሚደረግ ቅናሽ አንዱ ነው ያሉት ወ/ሪት ሩት ደንበኞችን ይበልጥ ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ሁለቱም ድርጅቶች ምርትና አገልግሎታቸውን የሚያስተዋውቁበት ትልቅ አጋጣሚ መሆኑንም አስረድተዋል።

**ኢትዮቴሌኮም የቴሌ ብር መተግበሪያን ከማዘመን ጋር ተያይዞ ተጨማሪ አዳዲስ አገልግሎቶችን ማካተት መጀመሩን አውስተው ከፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ጋር በአጋርነት ለመሥራት የሚያስችል አዲስ አሰራር ለመዘርጋት መታቀዱንም ማናጀሯ ይፋ አድርገዋል።**

ከፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ጋር በአጋርነት የሚሠራው ቴሌ ብር ለኩባንያው ደንበኞች ያቀረበው ይህ ልዩ ቅናሽም እጅግ ሳቢ ከመሆኑም ባሻገር የሁለቱን ድርጅቶች ወዳጅነት ለማጠናከር ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ያሉት ወ/ሪት ሩት ደንበኞች ላልተወሰነ ጊዜ በ6 ቱም የከገበሬው ሱቆች *127# ላይ በመደወል አልያም የቴሌብር መተግበሪያን ተጠቅመው ሲከፍሉ የከፈሉትን ገንዘብ 10 በመቶ ተመላሽ የሚያገኙበትን አሠራር ተግባራዊ እያደረገ በመሆኑ የከገበሬው ሱቅ ደንበኞች እና የድርጅቱ ሠራተኞች ቀላል፣ ምቹ እና ፈጣን የሆነውን መተግበሪያ በመጠቀም ጊዜና ወጪያቸውን ቆጥበው እንዲገበያዩ ግብዣቸውን አቅርበዋል።

## ለፐርፐዝብላክ ባለአክሲዮኖች ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ መረጃዎችን ተደራሽ የማድረግ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠሉ ተገለጸ።

የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የባለአክሲዮኖች ጉዳይ ክፍል ከዚህ ቀደም ይጠቀምበት የነበረውን የባለአክሲዮኖች ማስተናገጃ ሥርዓት በማሻሻል በተቀላጠፈ መንገድ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑንና ይበልጥ በዘመነ አሰራር ባለአክሲዮኖችን ተጠቃሚ ለማድረግ አቅጣጫዎችን አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ አስታውቋል።

የኩባንያውን የሥራ ክፍሎች አካሄድ በጥልቀት በማስረዳት ኢንቨስተሮች ስለፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ እንዲሁም ነባርና አዳዲስ ባለአክሲዮኖች በኢንቨስትመንቱ ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ መረጃን የማድረስና ሰርተፊኬቶችን የመስጠት ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠላቸው ተገልጿል።



**ክፍሉ በየጊዜው የሚፈጠሩ የቴክኖሎጂ መሻሻሎችን መሠረት ያደረገ የባለአክሲዮኖች መተዳደሪያ ሰነድ አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን በእጅ ስልኮቻቸው ከሚላኩ አጭር የጽሑፍ መልእክቶች በተጨማሪ ከኩባንያው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክፍል ጋር በመቀናጀት ባለአክሲዮኖችን የሚያሳትፉ የማኅበራዊ ትስስር ገጾችን በማበልጸግ ሐሳባቸውን በነጻነት የሚገልጹበትና ስለድርጅቱ አሠራር በቅርበት የሚያውቁበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ላይ መሆኑንም ይፋ ተደርጓል።**

ስለ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ተግባራት ትክክለኛና ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን በማጋራት ኢንቨስተሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በኩባንያው ላይ ያላቸውን እምነት ለማዳበር በትኩረት እየሠራ ይገኛል የተባለ ሲሆን ክፍሉ ከሁሉም የኩባንያው የሥራ ክፍሎች ጋር በተለይም ከማርኬቲንግ፣ ኮሙኒኬሽን እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር በመቀናጀት መረጃዎችን የማጋራትና የኩባንያውን የኢንቨስትመንት አማራጮች የማስተዋወቅ ሥራዎች እያከናወነ እንደሚገኝ ተነግሯል።

የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን አክሲዮን ሕጋዊነታቸው የተረጋገጠ ማናቸውም በብቸኛ ባለቤትነት ወይም በሽርክና የሚተዳደሩ የግል ኩባንያዎች፣ የብድር፣ የሙያ፣ የእድር እና ሌሎችም ማኅበራት እንዲሁም ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም መግዛት የሚችል ሲሆን ባለአክሲዮኖች የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ ተካፋይ ከመሆን ባሻገር በኩባንያው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአካልም ሆነ በወኪሎቻቸው አማካኝነት ድምጽ የመስጠት ሙሉ መብት ከዚያም ባለፈ በስብሰባዎችና ሌሎች ድርጅቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች እንዲሳተፉ ቀድሞ የማሳወቅ ሥራዎች በባለአክሲዮኖች ጉዳይ (ኢንቨስተር ሪሌሽን) ክፍል የሚተገበር መሆኑ ነው ይፋ የሆነው።

የባለአክሲዮንነት ማረጋገጫ አወሳሰድን በተመለከተም በሁለት ዓመት ውስጥ ቃል የገቡትን የአክሲዮን ገንዘብ ከፍለው ላጠናቀቁ ባለአክሲዮኖች የዋና ሥራ አስፈጻሚውና የክፍሉ ዳይሬክተር ፊርማ የሰፈረበት የማረጋገጫ ሰርተፊኬት በተቀላጠፈ መንገድ እየተረከቡ እንደሚገኙ ተገልጾ በቀጣይም በግለሰብም ሆነ በተቋም ደረጃ አክሲዮን በመግዛት ኩባንያውን ለሚቀላቀሉ ኢንቨስተሮች የኩባንያውን አጠቃላይ የኢንቨስትመንት አሰራር በተመለከተ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች በመረጃ የተደገፈ አጥጋቢ ምላሽ ለመስጠት የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የባለአክሲዮኖች ጉዳይ ክፍል ዝግጁ መሆኑ ተገልጿል።

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ለክላስተሮች ማደራጃ ብድር የሚያስገኘውን የጋራ መግባቢያ ሰነድ ፒስ ማይክሮ ፋይናንስ ከተሰኘው ተቋም ጋር ተፈራረመ።

በከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር አማካኝነት በመላው አገሪቱ የሚገኙ 1 ሚሊዮን ገበሬዎችን በ1000 ክላስተሮች በማደራጀት ባለአክሲዮን ለማድረግ እንዲሁም በመርሐግብሩ የሚካተቱ ገበሬዎችን ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚሠራው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ለክላስተሮች ማደራጃ የሚውል የብድር አገልግሎት ከሚሰጥ ፒስ ከተሰኘ የቁጠባና ብድር ተቋም ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙን የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ፓርትነርሺፕ ዳይሬክተር ወ/ሪት ኢየሩሳሌም አንተነህ አስታውቀዋል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የግብርናውን ዘርፍ በመደገፍ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ ባሻገር የገበሬዎችን ሕይወት የማሻሻልን ውጥን እውን ለማድረግ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጥምረት እየተንቀሳቀሰ ሲሆን ባሳለፍነው ሳምንትም በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ መሠረት የቁጠባና ብድር ተቋሙ በዋነኛነት በፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ለሚተገበረው የክላስተር ማደራጃና ማስፋፊያ መርሐ ግብር የሚውል ብድር ለመስጠት ስምምነት ላይ ደርሷል።

ምስል በኑብዩ ዳንኤል



“

**በስምምነት መርሐግብሩም ላይ የኩባንያውን ሥራ በማገዝና እና በማቀላጠፍ ለጥቁር ሕዝቦች ዘላቂ የኢኮኖሚ የበላይነት እዝከተለያዩ ተቋማት ጋር በጥምረት መስራት ገንዘብ፣ ጊዜ እንዲሁም የሰው እና የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ ከመጠቀም አንጻር እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ከመፍጠር አንጻር ትልቅ ሚና ይጫወታል ተብሏል።**

የቁጠባና ብድር ተቋሙ በተመረጡ ክላስተሮች ለተደራጁ ገበሬዎች ስልጠና መስጠትን ጨምሮ አስፈላጊ የሆኑ ሙያዊ እገዛዎችን እንደሚያደርግ የተጠቀሰ ሲሆን ተፈጥሯዊ ይዘታቸውን የጠበቁ ማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር፣ ጸረ ተባይ መድሃኒቶችና ሌሎችም የግብርና ግብአቶች አቅርቦት በማመቻቸት እንዲሁም ዘመናዊ የመስኖ ልማትን ለማበረታታት አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግም ተገልጿል።

የፒስ ማይክሮ ፋይናንስ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ተዘራ ከበደ እንደተናገሩት አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ ሲጠናቀቅ ተቋሙ የብድር አሰጣጥ ሒደቱን በተቀላጠፈ መንገድ የሚያከናውን ሲሆን በብድሩ የሚከናወኑ ሥራዎችን ባለሙያዎችን በመመደብ የሚከታተል መሆኑንም ገልጸዋል።

በቀጣይነትም በሁለቱም ድርጅቶች የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች አማካኝነት መረጃዎችን የመለዋወጥ ተግባሩ ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት የፐርፐዝብላክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ሁለቱም ተቋማት ለዜጎች የገንዘብ አቅምን በመፍጠር ዘላቂነት ባላቸው ሥራዎች አማካኝነት ራሳቸውን ችለው ማየትን ራዕይ አድርገው መንቀሳቀሳቸው የሚጋሩት ትልቅ ነጥብ መሆኑ ለስምምነቱ ይበልጥ ትርጉም ይሰጠዋልም ሲሉ አክለዋል።

ዋና አዘጋጅ፦ ሰላማዊት ደበበ
ሲንየር ሪፖርተር፦ ጌታባለው ገ/ሐና
ሪፖርተር፦ ኤደን ደነቀ

**ለበለጠ መረጃ**

ሰንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ

+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222

7151

www.purposeblackethiopia.com